የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# ነጻነታቸውን በተነፈጉ ሰዎች ዙሪያ የተደረገ ብሔራዊ ምርመራ



Photo Credit: Israel Solomon, Media and Communications Department, EHRC

## አንኳር ጉዳዮች

መጋቢት 2016 ዓ.ም.

www.ehrc.org

## አንኳር ጉዳዮች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት (አንቀጽ 55/14) የተቋቋመ ነጻ የፌዴራል መንግሥት አካል ነው። ኢሰመኮ በመቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) መሠረት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው።

በወንጀል ተጠርጥረው በመታሰር ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነው ነጻነታቸውን በተነፈጉ ሰዎች ላይ የሚደርስን ተቋማዊ እና ተደጋጋሚ የመብቶች ጥሰቶች ለመለየት እና ምክረ ሐሳቦች በማቅረብ የሰብአዊ መብቶች አያያዝን ለማሻሻል እንዲረዳ ኢሰመኮ በኢትዮጵያ ውስጥ በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን ብሔራዊ ምርመራ (National Inquiry) አከናውኗል።

ብሔራዊ ምርመራ ማለት ተቋማዊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመፍታት የሚውልና ሕዝብ የሚሳተፍበት የምርመራ ዘዴ ነው። ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ተቋማዊና ውስብስብ የሰብአዊ መብቶች ችግሮችን በማጥናት ለመፍትሔው የሚጠቅሙ ምክረ ሐሳቦችን ለማቅረብ ብሔራዊ ምርመራን ይጠቀማሉ። የብሔራዊ ምርመራ አንዱ አካል ለመገናኛ ብዙኃን ክፍት የሆኑ ግልጽ የአቤቱታ መቀበያ መድረኮች በመሆኑ ስለሰብአዊ መብቶች ግንዛቤን ለማሳደግ ጠቃሚ ነው። ከብሔራዊ ምርመራ የሚገኙ ግኝቶች እና ምክረ ሐሳቦች የሰብአዊ መብቶችን አፈጻጸም ለማሻሻል ጥቅም ላይ ይውላሉ።

የብሔራዊ ምርመራው ዓላማ የነጻነት መብት ጥሰቶችን መመርመርና መሰነድ፣ ተጎጂዎች የደረሰባቸውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እንዲናገሩ እንዲሁም አቤቱታ የቀረበባቸው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለጉዳዩ ምላሽ እንዲሰጡበት መድረክ መፍጠር፣ በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል የውይይት ዕድል ማመቻቸት፣ በዘፈቀደ እስራት መንስኤዎችና ችግሩን በሚያባብሱ እና በሚያወሳስቡ ሁኔታዎች ዙሪያ ግንዛቤ ማሳደግና እና የመፍትሔ ሐሳቦችን ማቅረብ ነው። ኢሰመኮ በዚህ ብሔራዊ ምርመራ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊ እና በቀድሞው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ ከሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. እያንዳንዳቸው 3 ቀን የወሰዱ 4 ሕዝባዊ የአቤቱታ መቀበያ መድረኮችን በማከናወን የብሔራዊ ምርመራውን ሥነ-ዘዴ፣ ቁልፍ ግኝቶች እና ምክረ-ሐሳቦች የያዘ ሪፖርት አዘጋጅቷል።

### የብሔራዊ ምርመራው ሥነ-ዘዴ

ብሔራዊ ምርመራው ርዕሰ ጉዳይ (ማለትም:- ነጻነታቸውን የተነፈጉ ሰዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ) የተመረጠው ኢሰመኮ ቀደም ሲል ከተጎጂዎች፣ ከቤተሰቦቻቸው፣ ወይም ከምስክሮች ተቀብሎ ካስተናገዳቸው አቤቱታዎች እንዲሁም በፖሊስ ጣቢያዎች፣ ማቆያ ማእከላት እና ማረሚያ ቤቶች ካደረጋቸው ክትትሎች ግኝቶች በመነሳት ነው።

የብሔራዊ ምርመራው የጊዜ ወሰን ከሚያዝያ 2010 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም. ባሉት አምስት ዓመታት የተገደበ ነበር። የምርመራው ከባቢያዊ ወሰን አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊ እንዲሁም የቀድሞው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎችን ያካተተ ሲሆን እነዚህም ክልሎች የተመረጡት በዋናነት በያዙት የሕዝብ ብዛት እና በሚሸፍኑት ሰፊ መልክአ ምድራዊ ወሰን ነው። የምርመራ ሂደቱም የምርመራውን ወሰን የሚለይ የመነሻ ጥናት /Preliminary Study/ ማከናወንን፣ የምርመራ ሂደት መምሪያ ሰነዶችን ማዘጋጀትን፣ ሀገር አቀፍ የማስጀመሪያ ዐውደ ጥናት ማከናወንን፣ መርማሪ ኮሚሽነሮችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን መሰየምን፣ እንዲሁም ሕዝባዊ መድረኮች ማዘጋጀትን ያካተተ ነበር።

የብሔራዊ ምርመራውን ሂደት መምሪያ ሰነዶች በዓለም አቀፍ ልምድና ምርጥ ተሞክሮዎች መሠረት የተዘጋጁ ሲሆኑ፤ እነዚህም የባለድርሻ አካላትን የመምረጫ መምሪያን፣ የግልጽ

አቤቱታ መቀበያ መድረክ መምሪያን፣ በማስረጃ መሪዎች ሊቀርቡ የሚገቡ ጥያቄዎች ዝርዝርን እና የፈቃደኝነት መግለጫ ቅጾችን ያካትታሉ። ሰነዶቹ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ብሔራዊ ምርመራ በማካሄድ ልምድ ባካበቱ ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ድጋፍና ግምገማ ጭምር የተዘጋጁ ናቸው።

### *መርማሪ ኮሚሽነሮች እና ሌሎች ባለሙያዎች*

የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ የመርማሪ ኮሚሽነሮችን ቡድን ሲያቋቁሙ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ራኬብ መሰለን፣ የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ኮሚሽነር ዶ/ር አብዲ ጅብሪልን እና የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ኮሚሽነር ርግበ ገብረሓዋሪያን እንዲሁም በምርመራው ወቅት የሴቶችና ሕፃናት መብቶች ኮሚሽነር የነበሩት መስከረም ገስጥን፣ በመርማሪ ኮሚሽነርነት በመመደብ የመርማሪ ኮሚሽነሮች ቡድን ተመሥርቷል። ይህ የመርማሪ ኮሚሽነሮች ቡድን በአማካይ 28 አባላትን ባቀፈ የባለሙያዎች ቡድን የተደገፈ ሲሆን የማስረጃ መሪዎች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ ራፖርተሮች፣ ድምጽ ቀጂዎች፣ የሎጂስቲክስ ኦፊሰሮች፣ የቋንቋ ተርጓሚዎች፣ የማስረጃ እና የሰነድ ኦፊሰር፣ የፕሮቶኮል ሠራተኞች፣ የፋይናንስ ኦፊሰሮች እና አስተባባሪዎች ይገኙበታል።

የኮሚሽነሮች ቡድን እና ባለሙያዎች (የብሔራዊ ምርመራ ቡድን) ስለ ብሔራዊ ምርመራ ስልቶችና አጠቃላይ ሂደት በዓለም አቀፍ የቴክኒክ ባለሙያ አማካኝነት ስልጠና በመውሰድና በተጨማሪም ከሌሎች ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የስልጠና ማኑዋሎች፣ ሪፖርቶች እና ሰነዶች መልካም ተሞክሮዎች በመቅሰም ለምርመራ ሥራው በቂ ዝግጅት አድረገዋል። የብሔራዊ ምርመራ ቡድኑ በኢሰመኮ አንኳር ዕሴቶችና መርሖች (ለእኩልነት፣ ለሰው ልጅ ክብር እና ፍትሕ ያለውን ቁርጠኝነት መሠረት ያደረገ ነጻነት/ገለልተኛነት፣ አካታችነት፣ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች እና ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍል ጋር አጋርነት እንዲሁም እውነተኛ እና ሥነ-ምግባር የተላበሰ ሥራ በሚሉት ዕሴቶችና መርሖች) በመመራት ሥራውን አከናውኗል። ***የፕሮጀክት ማስጀመሪያ ዐውደ-ጥናት***

የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. የብሔራዊ ምርመራውን ለማስጀመር ሀገር አቀፍ ዐውደ-ጥናት ተካሂዷል። የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች ከፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከክልል ፍትሕ ቢሮዎች፣ ከፌዴራልና ከክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ ከፌዴራልና ከክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽኖች፣ የነጻነት መብታቸውን በተነፈጉ ሰዎች ሰብአዊ መብቶች ላይ ከሚሠሩ የሲቪክ ማኅበራት፣ ከዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ፣ ከአውሮፓ ኅብረት የቴክኒክ ድጋፍ ክፍል፣ ከሚዲያ ባለሙያዎች እና ከኢሰመኮ ኮሚሽነሮች እና ሠራተኞች የተውጣጡ ናቸው። በዐውደ-ጥናቱ ላይ የብሔራዊ ምርመራውን አድማስ አስመልክቶ የተሳታፊዎችን ሐሳብና አስተያየት ለማሰባሰብ አጭር ጥናት ተካሄዷል። ምላሽ ሰጪዎቹ በተለይም ከቀድሞው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የመጡ ተሳታፊዎች ያለፍርድ ቤት ማዘዣ ተጠርጣሪን በቁጥጥር ሥር ማዋልን፣ ያልተመጣጠነ የኃይል እርምጃ መጠቀምን እና የእስረኞችን አያያዝ ሁኔታ የተመለከቱ ክፍተቶችን ጨምሮ ነጻነታቸውን በተነፈጉ ሰዎች መብቶች ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለይተው አውጥተዋል።

### *ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮች /Public Hearings/*

የብሔራዊ ምርመራው ወሳኝ ምዕራፍ ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮችን ማካሄድ ነው። በአራት ከተሞች ማለትም አዳማ፣ ባሕር ዳር፣ ጅግጅጋ እና ሃዋሳ ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮች የተዘጋጁ ሲሆን ከተሞቹ የተመረጡት በዋናነት ለተሳታፊዎች ባላቸው ምቹነት ነው። ተሳታፊዎቹ ተጎጂዎች፣ ምስክሮች፣ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ ምሁራን፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሲቪክ ማኅበራት ተወካዮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት

ነበሩ። የተመረጡትም የባለድርሻ አካላት መምረጫ መምሪያን እና የግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረክ መምሪያን መሠረት በማድረግ ነው።

ለእያንዳንዱ ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረክ ቅድመ ዝግጅቶችም ተደርገዋል። ባለድርሻ አካላት ነን የሚሉ ሁሉ በጉዳዩ ዙሪያ የተሠሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እና ሌሎች የምስክርነት ሰነዶችን ለኮሚሽኑ እንዲሰጡ ወይም እንዲያስገቡ ጥሪ ተደርጓል። ስለ ጉዳዩ በክልል እና በብሔራዊ ሚዲያዎች ገለጻ ተደርጓል። እንዲሁም የአቤቱታ መቀበያ መድረኩ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ በመድረኩ ከሚሳተፉ የክልል ተቋማት ኃላፊዎች እና ተወካዮች ጋር በየጽሕፈት ቤታቸው ውይይት ተደርጓል። ተጎጂዎች እና ምስክሮች በሚያቀርቡት የመብት ጥሰት ዓይነት፣ የጾታ፣ የአካባቢ ውክልና፣ የሃይማኖት፣ የአካል ጉዳት መጠን እና የተለያዩ ጉዳዮች ስብጥር በአግባቡ ለማካተት እንዲያስችል የምርመራ ቡድኑ ግልጽ የአቤቱታ መቀበያ መድረኩ ከመካሄዱ ቢያንስ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ የቅድመ-ማጣራት ሥራ ሠርቷል። በቅድመ ማጣሪያው ወቅት ከምስክርነታቸው ወይም ከጉዳያቸው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ማስረጃ ይዘው እንዲመጡ ተነግሯቸዋል። እንዳስፈላጊነቱም ኢሰመኮ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎችንም አሰባስቧል። ለተጎጂዎች እና ምስክሮች በግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኩ የሚሰጡት ምስክርነት ሊያስከትለው ስለሚችለው ውጤት ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፤ ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ምስክርነታቸውን የመስጠት አማራጭም ቀርቦላቸዋል። የግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኩ ከመጀመሩ በፊት በመረጃ ላይ የተመሠረተ የፈቃደኝነት መግለጫ ቅጹ ይዘት በሚረዱት ቋንቋ ከተብራራላቸው በኋላ ይህንኑ ቅጽ ሞልተው ፈርመዋል።

ከዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ምሁራን የተመረጡት ከግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮቹ በፊት ለኮሚሽኑ ባስገቡት የጥናት ጽሑፍ መሠረት ነው። የሀገር ሽማግሌዎች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች እና የሲቪክ ማኅበራት ተወካዮች በግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮቹ ላይ በይፋ ተጋብዘዋል። የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በዋናነት ከክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከማረሚያ ቤት ኮሚሽኖች፣ ከፖሊስ ኮሚሽኖች፣ ከሰላምና ጸጥታ ቢሮዎች፣ ከፍትሕ ቢሮዎች እና ከዞን ጽሕፈት ቤቶች የተውጣጡ እና አንዳንድ ጊዜም ከወረዳ ጽሕፈት ቤቶች የተውጣጡ በክልል መንግሥታት በኩል ጥሪ ተደርጎላቸዋል። ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮቹ የተካሄዱባቸው አካባቢዎች እና ክልሎች ስለብሔራዊ ምርመራው በቂ መረጃ እና ግንዛቤ እንዲኖራቸው መድረኩ ከመካሄዱ የተወሰኑ ቀናት አስቀድሞ ኢሰመኮ በሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ግልጽ የአቤቱታ መቀበያ መድረኩን አስተዋውቋል፤ ዓላማውን እና ሂደቱን አስረድቷል፤ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በሂደቱ እንዲሳተፉ እና የምርመራው ምክረ-ሐሳቦች ትግበራ ላይ በስፋት እንዲሳተፉ በማበረታታት ባስተላለፈው ጥሪ መሠረት ጥሩ ተሳትፎ ታይቷል።

እያንዳንዱ ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረክ በሦስት መርማሪ ኮሚሽነሮች የተመራ ነበር። ሁሉም መድረኮች በመርማሪ ኮሚሽነሮቹ ሰብሳቢ የመክፈቻ ንግግር የተጀመረ ሲሆን የመድረኮቹ ዓላማ እና ሂደት ገለጻ ተደርገዋል። በመድረኩ ፊት የቀረቡ ሁሉም ተጎጂዎች፣ ምስክሮች እና ሌሎች ተሳታፊዎች ከመመስከራቸው በፊት ቃለ-መሐላ ፈጽመዋል። በልዩ ሁኔታዎች በተለይ በሃይማኖታዊ እና በሌሎች ምክንያቶች ያለ ቃለ-መሐላ የተሰጡ ምስክርነቶች በሪፖርቱ በግልጽ ተመልክቷል።

እያንዳንዱ የግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረክ ለሦስት ቀናት የቆየ ሲሆን በመጀመሪያው አንድ ቀን ከግማሽ የተጎጂዎች እና ምስክሮች ምስክርነት ተሰምቷል። የሁለተኛው ቀን አጋማሽ ከሲቪክ ማኅበራት ተወካዮች፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከማኅበረሰቡ መሪዎች እና ከተመራማሪዎች ምስክርነት እንዲሁም የጥናትና የምርምር ውጤቶች ተሰምቶበታል። በሦስተኛው ቀን የመንግሥት ኃላፊዎች ምላሾቻቸውንና ማብራሪያዎቻቸውን እንዲሰጡበት እና ችግሩን ለመፍታት ወይም ለውጥ ለማምጣት ቃል እንዲገቡበት የተመደበ

ቀን ነበር። ምስጢራዊ አቤቱታ መቀበያ መድረክ ከግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኩ ጎን ለጎን ተካሂዷል። መርማሪ ኮሚሽነሮች በግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮች ማጠናቀቂያ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡ ሲሆን አንኳር ግኝቶችንና ምክረ-ሐሳቦችን አብራርተዋል።

በአጠቃላይ አራት ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮች የተካሄዱ ሲሆን የመጀመሪያው መድረክ በሃዋሳ ከተማ ከሰኔ 27 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም.፣ ሁለተኛው በጅግጅጋ ከተማ ከታኅሣሥ 10 እስከ ታኅሣሥ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. በሶማሊኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች በአስተርጓሚ በመታገዝ፣ ሦስተኛው ደግሞ በባሕር ዳር ከተማ ከመጋቢት 19 እስከ 21 ቀን 2015 ዓ.ም. እንዲሁም አራተኛው እና የመጨረሻው ከሚያዝያ 16 እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዳማ ከተማ በአፋን ኦሮሞ እና በአማርኛ ቋንቋዎች በአስተርጓሚ በመታገዝ ተከናውነዋል።

በግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮች በአጠቃላይ 365 ሰዎች (31 ሴቶች እና ሰባት አካል ጉዳተኞች) ተሳትፈዋል። በድምሩ 86 ተጎጂዎች እና ምስክሮች (ከጠቅላላው ተሳታፊዎች 24 በመቶ) ተሳትፈዋል። ከእነዚህም 66 ሰዎች በግልጽ፣ 20 ሰዎች ደግሞ በምስጢር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። በግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮች ላይ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተውጣጡ ስምንት ተመራማሪዎች እና ስምንት የሀገር ውስጥ እና አንድ ዓለም አቀፍ የሲቪል ማኅበራት ተወካዮች ተሳትፈዋል።

ግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮቹ የተካሄዱት ምንም ጉዳት ያለማድረስ መርሕ መሠረት ነው። የብሔራዊ ምርመራ ቡድኑ የግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮችን ከማካሄዱ በፊት የአደጋ ሥጋት ግምገማ በማካሄድ በተሳታፊዎች ላይ ሊደርስ የሚችሉ አደጋዎችን ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ወስዷል። መርማሪ ኮሚሽነሮች የመንግሥት ኃላፊዎችና ጽሕፈት ቤቶች የተጎጂዎችን እና ምስክሮችን ደኅንነት የመጠበቅ ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ እና በመድረኩ በሰጡት ምስክርነት ምክንያት የቂም-በቀል ጥቃት ወይም አጸፋዊ እርምጃዎች ወይም ድርጊቶችን ከመውሰድ እንዲቆጠቡ ተገቢው ጥንቃቄና ዝግጅት ተደርጓል። በግልጽ አቤቱታ መቀበያ መድረኮች ላይ በመመስከራቸው ምክንያት በተጎጂዎች እና ምስክሮች ላይ የሚፈጸሙ ወይም የሚሞከሩ የአካል ጉዳት፣ የትንኮሳ ወይም የማስፈራራት ድርጊቶችን የሚከታተል እና አቤቱታ ተቀብሎ የሚመረምር የኢሰመኮ ተወካይ ስም እና አድራሻ ተገልጿል። የብሔራዊ ምርመራ ቡድኑ በመንግሥት ኃላፊዎች የቂም በቀል እርምጃዎች ሊወሰዱብን ይችላሉ ብለው ሥጋታቸውን በገለጹ ተጎጂዎች ወይም ምስክሮች ላይ መደበኛ ክትትል አድርጓል።

የተጎጂዎች፣ ምስክሮች ወይም ሌሎች ተሳታፊዎች የምስክርነት ቃል በመንግሥት ኃላፊዎች በኩል በግልጽ ሲካድ፣ መርማሪ ቡድኑ ተጨማሪ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና በመመርመር ትክክለኛውን ሁኔታ አረጋግጧል።

### ቁልፍ ግኝቶች

አብዛኛዎቹ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙት በኃይል ግጭቶች ዐውድ፣ እንዲሁም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና በስድስተኛው አጠቃላይ ሀገራዊ ምርጫ ዐውዶች ውስጥ ነው። ኢሰመኮ በአማራ፣ በኦሮሚያ በሶማሊ እና በቀድሞው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ባካሄደው ብሔራዊ ምርመራ የሚከተሉትን የሰብአዊ መብቶች ችግሮች ለይቷል፡

- **ማሠቃየት እና ኢ-ሰብአዊ አያያዝ፡** ደብዛን አጥፍቶ ማሰርን፣ በግዳጅ መሰወርን፣ በእስር ቤቶች ውስጥ ክብርን ያልጠበቁ አካላዊ ፍተሻዎችን እና በቂ ምግብና ውሃ በሌላቸው፣ በተጨናነቁ፣ የንፅሕና እና የሕክምና አገልግሎት በሌላቸው ያልተሟሉ እስር ቤቶች መታሰርን ጨምሮ፤
- **የዘፈቀደ እስር፡** መደበኛ ባልሆኑ ቦታዎች ማሰርን፣ ያለፍርድ ቤት ማዘዣ በቁጥጥር ሥር ማዋልን፣ መብታቸውን የሚጠይቁ ግለሰቦችን ከድርጊቶቻቸው ለማስቆም

በተደጋጋሚ እና ለረጅም ጊዜ አስሮ ማቆየትን፣ የተጠርጣሪ ቤተሰብ አባላትን በምትክ ማሰርን፣ በአደራ እስረኛነት ሰበብ ፍርድ ቤት ሳያቀርቡ ለረዥም ጊዜ ማረሚያ ቤት ማቆየት፣ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዋስትና መብት በመጣስ ማሰርን እና መንግሥትን በፍትሐብሔር ጉዳዮች የከሰሱ ግለሰቦችን የማሰር ድርጊቶችን ጨምሮ፤

- **ከሕግ አማካሪ ጋር መገናኘትን መከልከል፦** ተጠርጣሪዎች በሚያዙበት ወይም በሚታሰሩበት ወቅት ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር እንዳይገናኙ መከልከልን ወይም በመንግሥት ወጪ የሕግ ምክር አገልግሎት አለመስጠትን ጨምሮ፤
- **የቤተሰብ ጉብኝት ክልከላ** ፤
- **ወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃት፣**
- **የመተዳደሪያ ገቢን ማጣት፤**
- **ስለ ስብአዊ መብቶች በቂ ግንዛቤ አለመኖር፣** እና
- **ለጥሰቶቹ መፍትሔ እና ማካካሻ አለመኖር** ናቸው።

አንዳንድ ጥሰቶች እና ችግሮች ተቋማዊ ከመሆናቸውም ባሻገር በብዙ ሰዎች ላይ በተደጋጋሚ የመፈጸም አዝማሚያን ያሳያሉ። የሰብአዊ መብቶች ጥሰቱ የተፈጸመው በሚሊሻ አባሎች፣ የቀበሌ አስተዳዳሪዎች፣ የመደበኛ ፖሊስ አባላት፣ በቀድሞው የልዩ ኃይል ፖሊስ አባላት፣ የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት፣ የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላት እና የመንግሥት ኃላፊዎች ነው።

## ምክረ-ሐሳቦች

### ለፌዴራል እና ክልል መንግሥታት

- የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ተገቢውን የተሟላ የወንጀል ምርመራ በማድረግ አስፈላጊውን አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ማድረግ፣
- ለተጎጂዎች ካሳ ለመስጠት የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋትና መተግበር፣

### ለፖሊስ

- “ምትክ እስር” በሚል ምክንያት የተጠርጣሪውን የቤተሰብ አባላት የማሰር ድርጊትን ሙሉ በሙሉ አለመኖሩን ማረጋገጥና ይህን መሰል ከሕግ ውጭ የሆነ እስር በሚፈጽሙ የፖሊስ አባላት ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ፣
- በሕግ በልዩ ሁኔታዎች ከሚፈቀደው በስተቀር ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ የማሰር ድርጊትን ሙሉ በሙሉ አለመኖሩን ማረጋገጥና ይህን መሰል ከሕግ ውጭ የሆነ እስር በሚፈጽሙ የጸጥታ አካላት ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ፣
- በሕግ በተመለከተው መሠረት ተጠርጣሪዎች የሚያዙበትን ምክንያት እና ዝም የማለት (ያለመናገር) መብታቸውን በሚረዱት ቋንቋ ማሳወቅን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤
- ተመጣጣኝ ኃይል እና መሣሪያ መጠቀምን ማረጋገጥ፤
- መደበኛ ባልሆኑ የማቆያ ማእከላት፣ የቀበሌ አስተዳደሮች ጽሕፈት ቤቶችን ጨምሮ፣ ተጠርጣሪዎችን ከማሰር መቆጠብ፤
- በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች በቤተሰቦቻቸው፣ በዘመዶቻቸው፣ በሃይማኖት መሪዎች እና በሕግ አማካሪ የመጎብኘት መብትን እንዲሁም የሕክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- ነጻነታቸውን የተነፈጉ ሰዎችን በሰብአዊ ክብር መያዝ፣ እንዲሁም የማሠቃየት ድርጊቶችን እና ያልተገቡ አያያዞች መወገዱን ማረጋገጥ እና የወንጀል ምርመራን ማቀላጠፍ፣
- ለፖሊስ አባላት በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ግንዛቤን የሚያሳድጉ እና ዐቅምን የሚያጎለብቱ ስልጠናዎችን መስጠት፣

- የዐቃብያነ ሕግ ምክሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣ እና
- የፍርድ ቤት ትእዛዞችን ያለ ምንም ልዩነት መፈጸም፡፡

**ለማረሚያ ቤቶች**

- የእስር ሁኔታዎችን ማሻሻል፣
- እስረኞች በቂ ምግብ፣ ሕክምና፣ ውሃ እና የንፅሕና መጠበቂያ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- የእስረኞችን መብቶች ጥሰት መመርመር እና የማረሚያ ቤት ፖሊሶችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ፣
- ለማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላት እና ሠራተኞች በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ስልጠናዎችን በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ፡፡
- ቤተሰቦች፣ ዘመዶች፣ የሃይማኖት አባቶች እና የሕግ አማካሪዎች እስረኞችን እንዲጎበኙ መፍቀድ እና በሰብአዊ ክብር ማስተናገድ (በጎብኚዎች ላይ በተለይም በሴት ጎብኝዎች ላይ በአካላዊ ፍተሻ ሰበብ የሚፈጸም ጾታዊ ትንኮሳን እና ጥቃትን መከላከል) እና
- እስረኞችን በዕድሜ፣ በጾታ እና በወንጀል ክብደት መለየት፡፡

**ለፍትሕ ሚኒስቴር እና ፍትሕ ቢሮዎች**

- የሰብአዊ መብቶች መርሖችን መሠረት ያደረገ የማረሚያ ቤቶች መከታተያ ስልት ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የሰብአዊ መብት የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ማጠናከር፣
- የፖሊስ ጣቢያዎችን፣ የማቆያ ማእከላትን እና ማረሚያ ቤቶችን ወቅታዊ ክትትል ማጠናከር፣ የክትትል ግኝቶችን እና ምክረ-ሐሳቦችን መስጠት እና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣
- በፍትሕ ዘርፍ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላትን የተቋም ዐቅም ማሳደግ፣
- የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ካሳ የሚያገኙበትን ሥርዓት መዘርጋት፡፡